# በትራንስፖርት ሚኒስቴር

# የትራንስፖርት ባለስልጣን

## የተሽከርካሪ ጥገና እና የአካል ለውጥ ስራ ጋራዥ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 669/2013

ነሐሴ 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አብዲሣ ያደታ ሙለታ

ዋና ዳይሬክተር

## 1. መግቢያ

የተሽከርካሪ ጥገና ተቋማት/ጋራዦች/ ደረጃ ምደባ ስታንዳርድ ወጥቶ በስራ ላይ በዋለበት ወቅት የተዘጋጀው የጋራዥ ደረጃና የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ አፈጻጸም መመሪያ በወቅቱ የነበረውን ክፍተት በማቃለል ረገድ ሰፊ ጠቀሜታ ያበረከተ ቢሆንም በአሁኑ ሰዓት በተለይ ከተሽከርካሪ ጥገና እና አካል ለውጥ ስራ ጋር በተያያዘ እየተፈጠረ ያለው የተወዳዳሪነት መንፈስ በማጠናከር እና የስራው እንቅስቃሴ መስፋፋት በ2004 ዓ.ም ተዘጋጅቶ በስራ ላይ በዋለው የአፈጻጸም መመሪያ ስራውን ለመከታተልና ለመቆጣጠር ረገድ ከፍተኛ የሆነ የመልካም አስተዳደር ችግር አስከትሎ መቆየቱ የሚታወቅ ነው።

በመሆኑም በዚህ ዘርፍ በተለይም ልዩ ትኩረት በሚያሻው የተሽከርካሪ እና የአካል ለውጥ ስራ ላይ በተሰማሩ ጋራዦች ላይ የተለየ ትኩረት በመስጠት በአሰራር መመሪያው ለእያንዳንዱ የጥገና/የአካል ለውጥ ስራ ጋራዡ የሚሰጠው 100% ፐርሰንት መስፈርቱን ማሟላት የሚለው ከፍተኛ የሆነ የመልካም አስተዳደር ችግር የነበረውና የሚሰጠው የሙያ ብቃት ማረጋገጫው ጊዜያዊና ቋሚ በማለት ይሰጥ የነበረው በዚህ ማሻሻያ መስፈርቱን 80 በመቶ ላሟላ በየዓመቱ የሚታደስ ተደርጎ እንዲሰጠው በሚለው ተስተካክሏል። የአፈጻጸም መመሪያ ላይ በስፋትና በግልጽ ተለይተው ያልተቀመጡት የሚመለከታቸው ክፍሎች ተግባርና ሀላፊነት' የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥና ዕደሳ አገልግሎት አሰጣጥ' የአገልግሎት ክፍያ ሁኔታ ጥፋተኛ ሆነው በሚገኙ ባለንብረቶች ላይ መወሰድ የሚገባው የቅጣት እርምጃ' የብቃት ማረጋገጫ አያያዝና አጠቃቀም ሁኔታ ለጠፋ ወይም ለተበላሸ የብቃት ማረጋገጫ ምትክ(ግልባጭ) አሰጣጥና የቅሬታ አቀራረብ ስርዓት በዚህ የአፈጻጸም መመሪያ ማሻሻያ ላይ በማያሻማ ሁኔታ ተቀምጧል። በተጨማሪም ለአካል ለውጥ ስራ የሚቀርቡ ተሽከርካሪዎች ብቃት ከሚረጋገጥባቸው መመዘኛዎች መካከል አንዱና ቀዳሚ የሆነው የተሽከርካሪ አገልግሎት ዘመን ገደብ ግልጽ በሆነ መልኩ በዚሁ የአፈጻጸም መመሪያ ላይ ተካትቶ እንዲቀርብ ተደርጓል።



አብዲሣ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

## ክፍል አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ"የተሽከርካሪ እና የአካል ለውጥ ስራ ጋራዥ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 669/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. አውጪ ባለስልጣን »

የፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 468/1997 አንቀጽ 7/2ተ መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል

### 3. ትርጓሜ

በዚህ የአሰራር መመሪያ ውስጥ በአዋጅ ቁጥር 468/97 እና አዋጅ ቁጥር 681/2002 የተጠቀሱት ትርጓሜዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በተጠቀሱት ቃላትና አረፍተ ነገሮች የሚከተሉት አረፍተ ነገሮች የሚከተሉት ትርጓሜዎች ይኖራቸዋል።

1. የተሽከርካሪ ጥገና ማለት፦ በተሽከርካሪ ላይ የሚታየውን የቴክኒክና የአካል ጉድለት ለማሟላት በየትኛዉም የተሽከርካሪ ክፍል ላይ የሚከናወን የማስተካከል ስራ ነው ::
2. የተሽከርካሪ አገልግሎት አካል ለውጥ(ቅርፅ) ስራ ማለት፦ ተሽከርካሪው ቀድሞ ካለው የአካል ዓይነት ወደ ህዝብ ወይም ወደ ደረቅ ጭነት ማመላለሻ ወይም ወደ ገልባጭ ወይም ወደ ፈሳሽ ጭነት ማመላለሻ ወይም ደግሞ ወደ ጎታች ተሽከርካሪነት ለመቀየር በተሽከርካሪዎች አካል ላይ የሚደረግ ለውጥ ነው።
3. የብቃት ማረጋገጫ ሰጪ አካል ማለት፦ የትራንስፖርት ባለስልጣንና በአዋጅ ቁጥር 468/1997 አንቀጽ 2 ተራ ቁጥር 27 ላይ የተገለጹት አካላት ናቸው።
4. የተሽከርካሪ ጠቅላላ ክብደት ማለት፦ የአንድ ተሽከርካሪ አክስሎች በድምሩ ሊሸከሙት የሚችሉት ከፍተኛው የክብደት መጠን ማለት ሲሆን ይኸውም በተሽከርካሪው አምራች ድርጅት የተወሰነ ሲሆን በሀገራችን የመንገዶች የመሸከም አቅም አንጻር የአክስል ክብደትን አስመልክቶ በተደነገገው ደንብ መሠረት የሚወሰን ነው።
5. የተሽከርካሪ ነጠላ ክብደት ማለት፦ ተሽከርካሪው ሳይጭን ተቀያሪ ጎማ ይዞ ፣ነዳጅ ቢያንስ 3/4ኛ የሆነ ሞልቶ ፣ክሪክ ፣መፍቻ፣ ሽራ፣ ገመድና አሽከርካሪው በተሽከርካሪው ውስጥ ሆኖ ተመዝኖ የሚገኘው የክብደት መጠን/ውጤት/ ማለት ነው።



Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1

አብዲዩ ያያ ሙሉታ
ዋና ዳይሬክተር

6. የተሽከርካሪ የመጫን አቅም ማለት፦ ተሽከርካሪው እንደ አገልግሎቱ ዓይነት ከጠቅላላ ክብደቱ ላይ ነጠላ ክብደት ተቀንሶ በሀገሪቱ የአክስል ፖሊሲ መሠረት የሚሠጠው የጭነት ልክ ነው።
7. የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማለት፦ ፈቃድ ሰጪው አካል ያወጣውን የተሽከርካሪ ጥገናና አካል ለውጥ ስራ ጋራዥ ደረጃ ምደባ መስፈርትን ሙሉ በሙሉ 80 በመቶ እና ከዚያ በላይ አሟልተው የተገኙ ጋራዦች/የጋራዥ ባለንብረቶች/ በደረጃቸው በተሽከርካሪ ጥገና /አካል ለውጥ ስራ ወይም በተሽከርካሪ እና አካል ለውጥ ስራ ላይ መሰማራት የሚችሉ ስለመሆኑ የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ ሆኖ በየዓመቱ የሚታደስ ይሆናል።
8. ጋራዥ ማለት፦ የተሽከርካሪ ጥገና ወይም አካል ለውጥ ወይም የተሽከርካሪ ጥገናና አካል ለውጥ እና ሌሎች የሞደፊክ ስራ የሚያከናውን ተቋም ማለት ነው።
9. የብቃት ማረጋገጫ መሰረዝ ማለት ፡- ተደጋጋሚ ወይም ከባድ ጥፋት በማጥፋቱ ምክንያት እርምጃ የተወሰደበት የጋራዥ ባለንብረት ሆኖ በአገዳ ወቅት በተመሳሳይ የስራ መስክ ላይ እንዳይሰማራ መከልከል ማለት ነው።
10. የተሽከርካሪ የሞደፊክ ስራ ማለት ፡- ከተራ ቁጥር 2 ውጭ ያሉ ሌሎች የጥገና እና የአካል ስራዎችን ማከናወን ማለት ነው።

## 4. የተፈጻሚነት ወሰን

ማንኛውም በጋራዥ ስራ ላይ በሚገኙ ተቋሚት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## 5. የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ስለማስፈለጉ፦

- ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም ድርጅት ወይም ግለሰብ ከፈቃድ ሰጪው አካል የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሣያገኝ የተሽከርካሪ ጥገናና አካል ለውጥ ስራ እንዲሁም ከተሽከርካሪ ጋር ተያያዥነት ያለው ጋራዥ ከፍቶ መስራት አይችልም።
- ማንኛውም ጋራዥ ወይም የአካል ለዉጥ የሚሰራ ድርጅት የተጋጨ ተሽከርካሪ ከመጠገኑ በፊት ባለንብረቱ ማረጋገጫ ደብዳቤ ከፖሊስ ማምጣቱን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል።

## ክፍል ሁለት

## 6. የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት አመልካቹ ማቅረብ የሚገባቸው መረጃዎች

1. አመልካቹ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ የተነሳው 2 ጉርድ የፓስፖርት መጠን ባለቀለም ፎቶግራፍ ማቅረብ፣



እብዲሣ ያደታ ሙላታ
ዋና ዳይሬክተር

2. የአመልካቹ ማንነት የሚገልጽ የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወይም የፀና የፓስፖርት ኮፒ ማቅረብ፣ወይም የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፍቃድ ያቀርባል ።
3. የንግድ ድርጅቱ ሙሉ አድራሻ፣ ክልል፣ ዞን፣ ክፍለ ከተማ/፣ ወረዳ፣ ቀበሌ፣ የስልክ ቁጥር፣ ፖ.ሳ.ቁጥር፣ ፋክስና ኢ-ሜይል /ካለ/፣
4. የድርጅቱ ባለቤት ወይም ስራ አስኪያጅ ስም እስከ አያት እና አድራሻ፣
5. የባለቤትነት ወይም ወኪልነት ሕጋዊ ማረጋገጫ ማቅረብ፣
6. ዕድሜ 18 ወይም በላይ የሆነ፣
7. አስፈላጊውን የአገልግሎት ክፍያ መፈጸም፣
8. ህጋዊ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ካርታና የኢንቨስትመንት ፈቃድ ወይም የመጋዘንና የመስሪያ ቦታ ካርታና ተሻሽሎ በቀረበዉ የተሽከርካሪ ጥገናና አካል ለውጥ ጋራዥ አገልግሎት መስጫ መስፈርት (STANDARD) ቁጥር ---/2011 ዓ.ም መሠረት የባለቤትነት ማረጋገጫ /በኪራይ ከሆነ ህጋዊ የኪራይ ውል ማስረጃ/ የሃይማኖት ተቋማት ከሆነ በማህተም የተረጋገጠ/ስነድ አልባ ሆኖ የሚመለከተዉ አካል የካርታ ሂደት ላይ መሆኑን የተገለፀበትን ማቅረብ፣
9. ተሻሽሎ በቀረበዉ የተሽከርካሪ ጥገናና አካል ለውጥ ጋራዥ አገልግሎት መስጫ መስፈርት (STANDARD) ቁጥር ---/2011 ዓ.ም መሠረት ለደረጃው የተሟላ የሰዉ ኃይልና የትምህርት ማስረጃቸዉን ፎቶ ኮፒ በድርጅቱ ማህተም በማረጋገጥ ከማመልከቻ ጋር አያይዞ ማቅረብ

## 7. የማመልከቻ አቀራረብና አዲስ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ

- **ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት ፣ ድርጅት ወይም ግለሰብ የተሽከርካሪ ጥገና/አካል ለውጥ ስራ ጋራዥ ከፍቶ ስራ ለመስራት ፦**

1. የብቃት ማረጋገጫ ሰጪው አካል ባዘጋጀው ፎርም መሠረት ባለጋራዡ አጠቃላይ የጋራዡን አደረጃጀት የተመለከተ መረጃ ሞልቶ ከማመልከቻው ጋር ያቀርባል። ጋራዡን ለማስገምገም ፕሮግራም ያስይዛል፤ በበቂ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር መረጃዎቹን ሞልቶ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ በ3 የስራ ቀናት ውስጥ ጋራዡን ማስገምገም አለበት።
2. የአገልግሎት ክፍያ የሚፈፀመው የጋራዡን አደረጃጀት ፎርም ሞልተው ባቀረቡበት ወቅት ይሆናል። ጋራዡ ሲገመገም የተጠየቀዉ መስፈርት የማያሟላ ሆኖ ሲገኝ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ያለተጨማሪ የአገልግሎት ክፍያ ለ2 ጊዚያት ብቃቱ ይገመገምለታል::
3. በግምገማው ውጤት መሠረት የሙያ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል።



አብዲሣ ያደታ ሙሰታ
ዋና ዳይሬክተር

4. ቦታው የግል ከሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ፤የኪራይ ከሆነ ደግሞ ቢያንስ ለአንድ ዓመት ህጋዊ የኪራይ ውል መቅረብ አለበት ።
5. የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት ተሻሽሎ በቀረበዉ የተሽከርካሪ ጥገናናአካል ለውጥ ጋራዥ አገልግሎት መስጫ መስፈርት (STANDARD) ቁጥር --/2011 ዓ.ም መሠረት ከጤንነት አጠባበቅ /ከደህንነትአኳያ/ የተቀመጠው መመዘኛ 100% በየደረጃው የተቀመጡ ጋራዥ ስታንዳርድ 80 በመቶ መሟላቱ ሲረጋገጥ ግምገማው በተጠናቀቀ ቢበዛ በ2ኛው የስራ ቀን በየዓመቱ የሚታደስ የብቃት ማረጋገጫ ይሰጠዋል ።
6. የሠው ኃይል ብዛትና የትምህርት ዝግጅት በስታንዳርዱ መሠረት መሟላቱ ተረጋግጦ የማወዳደሪያ አካል ይሆናል።
7. ስታንዳርዱን መሠረት አድረጎ በሚደረገው የግምገማ ውጤት መሰረት የጋራዡ አጠቃላይ ይዞታ በተቀመጠው መስፈርት መሠረት **80 በመቶ** እና ከዚያ በላይ ከተሟላ በየዓመቱ የሚታደስ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣል።

## 8. የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ስለማደስ

የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የተሰጠው ጋራዥ ፈቃድ በበጀት ዓመቱ ከሐምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 ድረስ ባለው ጊዜ የጋራዥ አደረጃጀት በእስታንዳርዱ መሠረት ተገምግሞ የተሟላ ሲሆን ይታደሳል ። በእደሳ ወቅት የቀድሞው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እና ማመልከቻ ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል።

## 9. <u>የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት አዘገጃጀት</u>

የሙያ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬቱ ላይ የብቃት ማረጋገጫ ሰጪው አካል ፊርማ እና ማህተም ፤የጋራዡ ስም እና የብቃት ማረጋገጫው ዓይነት የተሰጠበት ቀን የሚያበቃበትን ቀን በግልጽ ሊጠቀስ ይገባል'

## 10. <u>የሙያ ብቃት ማረጋገጫ አገልግሎት ክፍያን በተመለከተ</u>

1. በየዓመቱ የሚታደስ ጋራዥ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የተሰጠው የጋራዥ ባለንብረት /ህጋዊ ተወካይ/ ለብቃት ማረጋገጫ ሰጪው አካል ብር <u>1000.00</u> ይከፍላል።
2. የጋራዥ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ለማሳደስ የጋራዡ ባለንብረት /ህጋዊ ተወካይ/ ለብቃት ማረጋገጫ ሰጪው አካል ብር <u>500.00</u> ይከፍላል።
3. ለጠፋ ወይንም ለተበላሸ የጋራ» የሞያ የብቃት ማረጋገጫ ምትክ/ቅጂ/ ለማግኘት የጋራÿ ባለንብረት /ህጋዊ ተወካይ/ ለብቃት ማረጋገጫ ሰጪው አካል ብር <u>200.00</u> ይከፍላል ።



አብዲሣ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ... ሪፐብሊክ ትራንስፖርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport ... Authority No. 1

4. ለሁለተኛ ጊዜ ለጠፋ የጋራዥ ሞያ ብቃት ማረጋገጫ ሁለተኛ ቅጂ ለመውሰድ ብር 350.00 ይከፍላል።

5. የጋራዥ የሞያ ብቃት ማረጋገጫ የዕደሳ ጊዜውን አሳልፎ  የመጣ በያንዳንዱ ለቆየበት ወር ብር 100.00 ቅጣት ይከፈላል።

## ክፍል ሶስት

### የተለያዩ  አካላት ሥልጣንና ተግባር

### 11.የትራንስፖርት ባለሥልጣን ተግባርና ኃላፊነት

**ባለስልጣኑ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል ፦**

1. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የአሰራር መመሪያ እና ስታንዳርድ ማዘጋጀት ወይም ማሻሻል።
2. በጋራዥ ላሉ ባለሙያዎች ያላቸውን አሠራር ስልት እንዲያሻሽሉና ከዘመናዊ ቴክኖሎጂ ጋር እንዲተዋወቁ ስልጠና የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት።
3. በዚህ መመሪያ ላይ በተገለፀው መሰረት ወደ ህዝብ ማመላለሻ ወይም ወደ ደረቅ ጭነትና ገልባጭ ወይም ወደ ፈሣሽ ጭነት እንዲሁም ወደጎታች ተሽከርካሪነት የሚደረገውን የአካል ለውጥ ስራ ለማከናወን ብቁ ሆነው ለሚቀርቡ ጋራዦች በጋራዥ ምደባ ስታንዳርዱ መሰረት የሙያ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለተሰጣቸው ጋራዦች ዙሪያ ፣ቁጥጥር ማድረግ፣ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን መስጠት፣ ለክልል ትራንስፖርት ቢሮዎችና ለሁለቱ መስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮዎች ድጋፎችን ማድረግ፣ ከክልል ትራንስፖርት ቢሮዎችና ለሁለቱ መስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮዎች ጋር በመሆን የእርምት እርምጃዎችን መውሰድ ይችላል።
4. የክልል ትራስፖርት ቢሮዎች እና ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች የጋራዥ ባለቤቶች በተሰጣቸው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መሰረት ስለመስራታቸው ቁጥጥር ማድረጋቸውን ይከታተላል፣ድጋፍ ያደርጋል። ባለስልጣኑ በራሱ ባለሙያ የተወሰኑ ተቋማትን ለናሙና መርጦ በመገምገም በአፈጻጸሙ ላይ የክልል ትራ/ቢሮ ፣ ቅ/መ/ቤቶች እና የጋራዥ ባለቤቶች ጋር ይመክራል ፤የማስተካከያ እርምጃ እንድወሰድ ያደርጋል።
5. የጋራዥ የሙያ የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸውን እንዲሁም በየወቅቱ በክትትልና ቁጥጥር ከብቃት ማነስ ወይም በአፈጻጸም ጉድለት ምክንያት ከአገልግሎት የታገዱ ወይም የተሰረዙትን ጋራዦች ዝርዝር በመከታተል ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት በመረጃ መረብ ግንኙነት ወይም በወጥነት በሚዘጋጅ ፎርም በፋክስ በማስተላለፍ እንዲያውቁት ማድረግ።



አብዲሣ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

6. በጋራዥ ውስጥ ያለአግባብ የቆሙ ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ መረጃ ሲደርሰው ዝርዝሩን በመያዝ ተገቢ ክትትል ማድረግ።
7. የሙያ የብቃት ማረጋገጫ ያገኙ ጋራዦች የሚሰጡትን አገልግሎት መረጃ ማሰባሰብ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት
8. ወደ ሃገር ውስጥ በሚገቡ አዳዲስ የአውቶሞቲቭ ቴክኖሎጂዎች ዙሪያ የክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች እና ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች እንዲሁም የጋራዥ ሙያተኞች ስልጠና የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት
9. በሀገር አቀፍ ደረጃ የተሽከርካሪ ጥገና / የአካል ለውጥ ለማድረግ የሚያስችል ፖሊሲ መቅረጽና ለትግበራ ለሚመለከታቸው ማስተላለፍ
10. የልምድ ልውውጥ መድረክ በበጀት ዓመቱ መጠናቀቂያ ላይ የክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች እና ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች እንዲሁም የጋራዥ ሙያተኞች ጋር በማዘጋጀት የስራ ማሻሻያ ማድረግ
11. የአካል ለውጥ ለሚያስፈልጋቸው ተሽከርካሪዎች ዲዛይንና እስፔሲፊኬሽን በማዘጋጀት የክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች እና ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች እንዲሁም ለጋራዥ ባለቤቶች ማስተላለፍ

**12. የክልል ትራንስፖርት ቢሮዎችና የከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት**

1. የአካል ለውጥ ተሠርቶላቸው የሚቀርቡ ተሽከርካሪዎች ምዝገባ፦
   i. ህጋዊ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ በተሰጠው ጋራዥ ውስጥ የተሰሩ መሆናቸውን እና የሙያ የብቃት ማረጋገጫው ፈቃድ የታደሰ መሆኑን ማረጋገጥ
   ii. የአካል ለውጥ የተሰራለት ተሽከርካሪ የአገልግሎት ዘመኑ ያላለፈ እና በፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን የተሽከርካሪ አገልግሎት አሰጣጥ እና ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሠራር መመሪያ ቁጥር-19/2010 ዓ.ም እና ከዚያ በኃላ በወጡት የጭነት ልክ ውሳኔዎች መሠረት እንዲቀየር የተፈቀደ የተሽከርካሪ ሞዴል መሆኑን ማረጋገጥ፣
   iii. ተሽርካሪው በተዘጋጀው ዲዛይንና እስፔሲፊኬሽን መሠረት የተሠራ፣ የቴክኒክ ብቃቱና ምቾቱ ለተሰራለት አገልግሎት አይነት ብቁ መሆኑን ማረጋገጥ፣
   iv. የተሽከርካሪው ባለንብረት እና ባለጋራዡ የተዋዋሉበት ፎርም እና የግዴታ ውል መቅረቡን በማረጋገጥ እና በመመሪያ ላይ ከተሽከርካሪ ጥገና / አካል ለውጥ ወይም ጥገናና አካል ለውጥ እና ሞደፊክ ስራ ጋር በተያያዘ ለሚሰጠው አገልግሎት መቅረብ ይገባቸዋል ተብለው የተዘረዘሩትን መረጃዎች መቅረባቸውን በማረጋገጥ የተጠየቀውን የአገልግሎት ማመልከት።



አብዲሳ ያደታ ሙሊሳ
ዋና ዳይሬክተር

Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Transport Authority

v. ማንኛውም አካል ለውጥ የሚደረጉ ተሽከርካሪዎች ከነበረበት አገልግሎት ማለትም ከጭነት ወደ ሕዝብ፣ ከጭነት ወደ ቦቴ፣ ከቦቴ ወደ ጭነት የመሳሰሉትን የይዘት ለውጥ ሲያደርጉ ለባለሥልጣኑ ለውጥ ስለመደረጋቸው ማሳወቅ ይጠበቅበታል።

2. ድንገተኛ ቁጥጥር በማድረግ ህጋዊ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሣይሰጠው የተሽከርካሪ ጥገና ወይንም አካል ለውጥ ወይም ሞደፊክ ስራ የሚያከናውን ጋራዥ ሲያጋጥም በጋራዡ ላይ እርምጃ መውሰድ እና ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ሪፖርት ማድረግ፡-
3. ከጋራዦች አሰራር ጋር ተያይዞ የሚታዩ የአሰራር ችግሮች ሲያጋጥሙ አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ መውሰድና መረጃውን በወቅቱ ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ማስተላለፍ፡
4. የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸውን ጋራዦች ዝርዝር እና ልዩ ልዩ መረጃዎችን ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በወቅቱ ማስተላለፍ፤
5. በክልሉ ውስጥ ባሉ ጋራዥች ለጥገና ብለው ገብተው ከ 3(ሶስት) ወር በላይ ያለአግባብ የቆሙ ተሽከርካሪዎችን መዝግቦ መከታተል፣ሲጠየቅም መረጃ መስጠት።
6. በክልሉ ውስጥ በሚገኙ የጋራዥ ሰራተኞች/ሞያተኞች/ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት
7. በክልሉ ውስጥ ለሚገኙ ጋራዦች በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት የብቃት ማረጋገጫ መስጠት
8. የጋራዥ ደረጃና ሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለተሠጣቸው ጋራዦች ገምግሞ ፈቃዳቸውን ማደስ።
9. ደረጃቸውን ለማሻሻል ጥያቄ የሚያቀርቡ ጋራዦችን በመመዘኛው መሠረት በመገምገም አሟልተው ሲገኙ ደረጃቸውን ማሣደግ።
10. ማንኛውም የጋራዥ አገልግሎት የአካባቢን የትራፊክ ፍሰት በማያስናክልና የህብረተሰቡን ጤና የማያውክ መሆኑን ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት መከታተልና ማረጋገጥ

## 13. የጋራዥ ባለንብረት ተግባርና ኃላፊነት

1. በጋራዡ ውስጥ አገልግሎት ከመጀመሩ በፊት ተገቢውን የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ከፈቃድ ሰጪው አካል ከወሰደ በኋላ የንግድ ፈቃድ ከሚመለከተው አካል ማግኘት አለበት።
2. በተሰጠው የጋራዥ ደረጃና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መሠረት ብቻ አገልግሎት መስጠት።
3. በዚህ መመሪያ ላይ በአንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 19.1-19.6ላይ የተገለፀውን የተሽከርካሪዎች አገልግሎት ዘመን ጠብቆ የአካል ለውጡን መስራት።
4. ባለስልጣኑ በጭነት ልክ አወሳሰን በፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን የተሽከርካሪ አገልግሎት አሰጣጥ እና ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሠራር መመሪያ ቁጥር-19/2010 [illegible] በወጡ



አብዲሣ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

መመሪያዎች ላይ በዝርዝር ካስቀመጣቸው ሞዴሎች ውጭ የሆኑ ተሽከርካሪዎች ለአካል ለውጥ ሲቀርቡ በቅድሚያ መረጃውን ለባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ ማሣወቅና የጭነት ልኩ ተወስኖ ሲፈቀድ ብቻ የአካል ለውጡን መስራት።

5. የአካል ለውጥ ስራውን ከማከናወኑ በፊት ተሽከርካሪው ከዕዳ፣ ዕገዳ እና ቀረጥ ነፃ መሆኑን ከፋይሉ/ከኮምፒውተር ማረጋገጥ።
6. ለተሽከርካሪው ሞዴል በፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን የተሽከርካሪ አገልግሎት አሰጣጥ እና ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አሠራር መመሪያ ቁጥር-19/2010 ዓ.ም እና ከዚያ በኃላ በወጡት የጭነት ልክ፣ ዲዛይንና ስፔስፊኬሽን ጠብቆ የአካል ለውጡን መስራት።
7. ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል የጋራዡን የብቃት ማረጋገጫ በወቅቱ ማሣደስ
8. የአካል ለውጥ ለማሰራት ተሽከርካሪውን ይዞ ለሚቀርብ ባለንብረት በአካል ለውጡ ዙሪያ ያሉትን አጠቃላይ መረጃዎች በግልጽ ማስረዳት ይኖርበታል።
9. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ወይም ትራንስፖርት ቢሮዎች ወይም ትራንስፖርት ቅርንጫፍ መ/ቤቶች ለድጋፍና ለክትትል የሚያሠማራቸውን ሠራተኞች ተቀብሎ አስፈላጊውን መረጃ መስጠት።
10. የጋራዡን የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ለሌላ ማንኛውም ዓይነት ጋራዥ አሣልፎ መስጠት የለበትም።
11. በጋራዡ ውስጥ ተጠግነውም ሆነ የአካል ለውጥ የተሠራላቸውን ተሽከርካሪዎች መረጃ መያዝና በየወሩ እና በተጠየቀበት ጊዜ ለፈቃድ ሰጪው አካል በሪፖርት ማሣወቅ።
12. የብቃት ማረጋገጫውን በሚያወጣበት ወቅት ያቀረባቸውን አጠቃላይ የሰው ኃይል፣ የስራ መሣሪያ፣ የቦታ እና የጤና መመዘኛዎች በማንኛውም ሰዓት አሟልቶ መገኘት አለበት። ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ምክንያት የሚጓደሉ ካሉ መስፈርቱን ጠብቆ ምትክ ማሟላት አለበት።
13. ተሽከርካሪውን በሚሰራበት ወቅት በተሽከርካሪው ላይ ማንኛውም አይነት ጉዳት እንዳይደርስ ተገቢውን ጥንቃቄ ሁሉ ማድረግ ይጠበቅበታል።
14. ማንኛውም የጋራዥ ባለንብረት በስራው ዙሪያ ግልጽ ያልሆነ ነገር ሲገጥመው ስራውን ከመጀመሩ በፊት ከፈቃድ ሰጪው አካል ተጨማሪ መረጃ መጠየቅ ይኖርበታል።
15. በማንኛውም ሠዓት ፈቃድ ሰጪው እና የሚመለከተው አካል ለሚያቀርባቸው ጥያቄዎች ምላሽ /መረጃ/ መስጠት ይኖርበታል።
16. ለንብረቱና ለሠራተኞች ኢንሹራንስ መግባት።
17. በተለያዩ ምክንያቶች በጋራዡ ውስጥ ያለአግባብ ከ3 ወር ወይም ዉል ከተዋዋሉበት ከ1 ወር በላይ የቆሙ ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ ለፈቃድ ሰጪው አካል በወቅቱ ማሳወቅ ።



አብዲሣ ያደታ ሙሊት
ዋና ዳይሬክተር

18. የተሽከርካሪ አካል ለውጡን ስራ ከመጀመሩ በፊት ከተሽከርካሪው ባለንብረት ጋር የውል ፎርም መፈራረም አለበት።
19. ተሽከርካሪውን ሰርቶ ካጠናቀቀ በኋላ የንግድ ስራ ፈቃድ ኮፒ ፣የብቃት ማረጋገጫ ኮፒ፣ የውለታ ፎርም ኮፒ፣በጋራዡ ማህተም የተረጋገጠ ከማረጋገጫ ደብዳቤ ጋር አያይዞ ለተሽከርካሪው ባለንብረት መስጠት።ተሽከርካሪው በዲዛይንና ስፔስፊኬሽን መሠረት ስለሞኑ ከምዝገባ በፊት የሚረጋገጥ በመሆኑ በመመሪያ መሠረት መስራት ፣ትራንስፖርት መ/ቤት ከባለንብረቱ ጋር በአካል ቀርቦ ተሽከርካሪውን ማስመዝገብ አለበት።
20. ለጥገና የሚቀበላቸውን ተሽከርካሪዎች በተገቢው መንገድ የመረከቢያ ፎርም ሞልቶ በመመዝገብ /የሚወስደው ጊዜ ተጠቅሶ/ ለባለንብረቱ ማረጋገጫ በመስጠት መረከብና ጥገናው ሲጠናቀቅ የማስረከቢያ ፎርም አስፈርሞ ማስረከብ "ይኖርበታል።
21. የአገልግሎት ዋጋው በቅድሚያ ለደንበኛው ተገልፆ በሂደትም የሚኖሩ ተጨማሪ ወጪዎች ለደንበኛው እንዲያውቀው በማድረግ በግልጽነትና ታማኝነት አገልግሎቱን መስጠት።
22. ለጥገና አገልግሎት እንደ ግብአት የሚጠቀመው የመለዋወጫ እቃ ኦርጂናል መሆኑን ማረጋገጥ።
23. ማንኛውም የጥገና ወይም የአካል ለውጥ ስራ በህብረተሰቡ ጤናም ሆነ በአካባቢ ላይ ጉዳት በማያስከትል መልኩ (በተገቢው ጥንቃቄ) መከናወኑን ማረጋገጥ አለበት።
24. ተገቢው የጋራዥ ብቃት ማረጋገጫ ኖሮት ተሽከራካሪዎች በግጭትም ሆነ በግልበጣ አደጋ ለጥገና ወደ ገራዥ በሚመጡበት ወቅት ስራ ከመጀመሩ በፊት ከፍቃድ ሰጪው አካል ፍቃድ ማግኘት ይኖርበታል።

**14.የተሽከርካሪው ባለንብረት /ህጋዊ ተወካይ ተግባርና ኃላፊነት**

1. በተሽከርካሪ ጥገና እና አካል ለውጥ ስራ ዙሪያ አስፈላጊ የሆኑትን መሠረታዊ መረጃዎችን ከትራንስፖርት ባለስልጣን ዌብ ሳይት፣ከጋራዥ ባለንብረቶች እና የትራንስፖርት መ/ቤቶች ጠይቆ መረዳት ይኖርበታል።
2. ጥገና ወይም አካል ለውጥ ስራ እንዲሰራለት የሚያቀርበውን ተሽከርካሪ የተመለከተ ማንኛውንም ዓይነት በፋይሉ/በኮምፒውተር የተመዘገበ ዕዳ ፣ እገዳ ወይም ቀረጥ ነጻ ካለ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች ፈቃድ ማቅረብ አለበት።
3. ተሽከርካሪውን ህጋዊ በሆነና የታደሰ የብቃት ማረጋገጫ ባለው ጋራዥ ውስጥ ብቻ ማሰራት ይኖርበታል።



አብዲሣ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

4. የተሽከርካሪ ጥገና / አካል ለውጥ ስራ ከመጀመሩ በፊት ከጋራዡ ባለንብረት ጋር የውለታ ፎርሙን መፈራረም ይኖርበታል
5. ተሽከርካሪው በዲዛይንና በስፔስፊኬሽኑ መሠረት አልተሰራም ብሎ ካሰበ ተሽከርካሪው ከመረከቡ በፊት ለፈቃድ ሰጪው አካል ማሣወቅ ይኖርበታል።
6. ከተዘጋጀው ስታንዳርድ እና መመሪያ ውጪ ተሽከርካሪው እንዲሰራ ከጋራዡ ባለንብረት ጋር ማንኛውንም አይነት ስምምነት በማድረግለሚፈጠረው ችግር ኃላፊነቱ የባለጋራዡና የባለንብረቱ ይሆናል።
7. ጥገና ወይም አካል ለውጥ ስራ የተሠራለትን ተሽከርካሪ ይዞ ለምዝገባ ሲቀርብ ፣ ከባለጋራዡ ጋር ውለታ የገባበትን ፎርም እና የባለጋራዡን የብቃት ማረጋገጫ (የታደሰ) አሟልቶ መቅረብ ይኖርበታል።
8. ጋራዥ ያስገባውን ተሽከርካሪ በአግባቡ በመከታተል በቀጠሮው መሰረት ጥገና / አካል ለውጥ ስራ ወይም ጥገናና አካል ለውጥ ስራ መጠናቀቁን በማረጋገጥ መረከብ ይኖርበታል።
9. ለጥገና ወይም ለአካል ለውጥ ስራ ወይም ለጥገናና ለአካል ለውጥ ስራ ጋራዥ የሚያስገባውን ተሽከርካሪ በህጋዊ መንገድ በሰነድ ማስረከብና ጥገናው ሲጠናቀቅም አስፈላጊውን የአገልግሎት ክፍያ በመፈጸም በህጋዊ መልኩ መረከብ ይኖርበታል።

## 15.የሙያ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት አጠቃቀምን በተመለከተ

1. የሙያ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ኮፒ ተደርጎና በጋራዡ ማህተም ተረጋግጦ ለዕይታ ግልጽ በሆነ ቦታ ላይ በጋራዥ ውስጥ መቀመጥ/መሰቀል/ አለበት።በተጠየቁም ጊዜ ዋናውን /ኦርጅናሉን/ ማሳየት መቻል አለበት።
2. የሙያ የብቃት ማረጋገጫው ሰርተፍኬት ላይ ስርዝ ድልዝ የሚታይበት ከሆነ ተቀባይነት አይኖረውም።
3. የሙያ የብቃት ማረጋገጫው ሰርተፍኬት ፎቶ ኮፒ በጋራዡ ማህተም እስካልተረጋገጠ ድረስ እንደህጋዊ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም።
4. ያልታደሰ የሙያ የብቃት ማረጋገጫ ዋጋ አይኖረውም።

## 16.ለጠፋ ወይንም ለተበላሸ የሙያ የብቃት ማረጋገጫ ምትክ/ቅጂ/ አሰጣጥ

1. የሙያ የብቃት ማረጋገጫው የጠፋበት የጋራዥ ባለንብረት/ህጋዊ ተወካይ/ የሙያ ብቃት ማረጋገጫው የጠፋበት ለመሆኑ በጽሁፍ ማመልከቻ አስደግፎ ጥያቄ በማቅረብ በትክክል



አብዲሣ ያደታ ሙሉታ
ዋና ዳይሬክተር

Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Transport Authority No. 1

ስለመጥፋቱ የማረጋገጫ ፎርም ሲሞላና ምትክ/ቅጂ/ ለማግኘት የተቀመጠውን ክፍያ ሲከፍል የብቃት ማረጋገጫው ቅጂ የሚል ተጽፎበት ይሰጠዋል።

2. የሙያ የብቃት ማረጋገጫው የተበላሸበት የጋራዥ ባለንብረት /ህጋዊ ተወካይ/ የተበላሸውን የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት በመመለስ ምትክ እንዲሰጠው በማመልከቻ ጥያቄ ሲያቀርብና ምትክ /ቅጂ/ ለማግኘት የተቀመጠውን ክፍያ ሲከፍል ቅጂ የሚል ተጽፎበት የሞያ ብቃት ማረጋገጫው ይሰጠዋል።

3. ለሶስተኛ ጊዜ የሙያ የብቃት ማረጋገጫ ጠፋብኝ በማለት ቅጂ የማግኘት ጥያቄ ሲቀርብ እንደ አዲስ የጋራዥ ብቃት ማረጋገጫ ጥያቄ ተገምግሞ ይስተናገዳል።

## ክፍል አራት

### መስፈርት ፡ ልዩ ልዩ ድንጋጌ

### 17.የአካል ለውጥ የሚሰራላቸው ተሽከርካሪዎች ዕድሜ ገደብን በተመለከተ

1. ከጭነት ወደ ህዝብ ማመላለሻ ሊቀየሩ/ሊቀጠቀጡ/ የሚችሉት ከ7 ዓመት በላይ በሀገር ውስጥ በጭነት ተሽከርካሪነት አገልግሎት ያልሰጡ ተሽከርካሪዎች እና በውጭ ሀገር ከ10 ዓመት በላይ በጭነት ተሽከርካሪነት አገልግሎት ያልሰጡ ተሽከርካሪዎች ብቻ ናቸው።

2. ከሌሎች አገልግሎቶች ወደ ፈሳሽ ጭነት ሊቀየሩ የሚችሉት ተሽከርካሪዎች ከደረቅ ጭነት ወደ ነዳጅ ቦቴ የአካል ለውጥ የሚደረጉ ተሽከርካሪዎች ፈቃድ አሰጣጥ ለመቆጣጠር የወጣ የአሰራር መመሪያ ቁጥር 01/2001 መሠረት ከተመረቱበት ጊዜ ጀምሮ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር **ከ6 ዓመት** በላይ አገልግሎት ያልሰጡተሽከርካሪዎች ብቻ ናቸው።

3. ከሌሎች አገልግሎቶች ወደ ጎታች ሊቀየሩ የሚችሉት ተሽከርካሪዎች በገልባጭ ወይም በደረቅ ጭነት አገልግሎት ለመለወጥ ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ አድርጎ ብቁ ከሆነ የአገልግሎት ለውጡን ማግኘት ይችላል።

4. ከህዝብ ማመላለሻነት ወደ ደረቅ ጭነት፣ገልባጭና ጎታች ተሽከርካሪነት የሚደረግ የአካል ለውጥ ዓመታዊ የተሽከርካሪዎች ቴክኒክ ብቃት ምርመራ ያለፈ በማንኛውም የአገልግሎት ዘመን ላይ ተግባራዊ ሊደረግ ይችላል።

5. ከሌሎች አገልግሎቶች ወደ ደረቅ ጭነት ወይንም ገልባጭ ተሽከርካሪዎች የአካል ለውጥ ዓመታዊ የተሽከርካሪዎች ቴክኒክ ብቃት ምርመራ ያለፈ ተሽከርካሪ መስተናገድ ይችላሉ።



አብዲሣ ያደታ ሙሉታ
ዋና ዳይሬክተር

6. የአገልግሎት ዘመኑ ሲሰላ የተሽከርካሪው የስሪት ዘመን መነሻ ተደርጎ የሚቆጠር ሲሆን የአገልግሎት ዘመኑ በግልጽ በመረጃ ላይ ያልተገለጸ ተሽከርካሪ የአገልግሎት ጊዜውን ለማስላት አስቸጋሪ ስለሚሆን ይሄ ሁኔታ ከቴክኒክ ብቃት ማነስ ጋር ተያይዞ ለሚከሰት የህይወት እና ንብረት ውድመት አስተዋጽኦው ከፍተኛ በመሆኑ ወደ ደረቅ ጭነትና ገልባጭ አካል ካልሆነ በስተቀር ወደሌሎቹ የተሽከርካሪ አካል አይነቶች መቀየር አይቻልም።

## 18.ቅሬታ ስለማቅረብ

ማንኛውም አካል በትራንስፖርት ባለስልጣን ወይም በትራንስፖርት መሥሪያ ቤቶች የቅሬታ አቀራረብ ስርዓት መሠረት ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል።

## 19.መመሪያውን ስለማሻሻል

ትራንስፖርት ባለስልጣን አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማንኛውም ጊዜ ይሄንን መመሪያ የማሻሻል/የመለወጥ ስልጣን አለው።

## 20.መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ጸድቆ ከወጣበት የካቲት------ቀን 2011 ዓ. ም ይሆናል።

አብዲሣ ያደታ

የፌደራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን

ዋና ዳይሬክተር

## አባሪ

### 21. የቅጣት እርምጃ አወሳሠድ

በዚህ መመሪያ ላይ አንቀፅ 15 ስር በዝርዝር የተገለፁትን ተግባርና ሃላፊነቶች ተላልፎ ሲሰራ የተገኘ የጋራዥ ባለንብረት ከዚህ በታች በተገለፀው ሰንጠረዥ መሠረት እርምጃ የሚወሰድበት ሲሆን ፈቃድ ሰጪው አካል ከሚወስድበት እርምጃ በተጨማሪ እንደጥፋቱ ዓይነት በህግ ተጠያቂ ሊደረግ ይችላል፡፡

## 21.1. ጥፋተኛ ሆነው በሚገኙ የጋራዥ ባለንብረቶች ላይ የሚወሰድ የቅጣት እርምጃ

| ተ.ቁ | የጥፋት ዓይነት /ዝርዝር/ | በመጀመሪያ ጥፋት የሚወሰድ እርምጃ | በሁለተኛ ጊዜ ለሚፈፀም ጥፋት የሚወሰድ እርምጃ | በሦስተኛ ጊዜ ለሚፈፀም ጥፋት የሚወሰድ እርምጃ | በአራተኛ ጊዜ ለሚፈፀም ጥፋት የሚወሰድ እርምጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ተገቢውን የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ከፈቃድ ሰጪው ሳያገኙ በተሽከርካሪ ጥገና እና አካል ለውጥ ስራ ላይ ተሰማርቶ መገኘት | - የመጀመሪያ ደረጃ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የተሰራው ስራ ስታንዳርዱን የጠበቀ ከሆነ ብቻ የምዝገባ አገልግሎት መስጠት | በህግ አገልግሎት በኩል ክስ እንዲመሰረት ማድረግ | | |
| 2 | ለጋራዡ ከተሰጠው የተሽከርካሪ ጥገና/አካል ለውጥ ስራ ደረጃና የሙያ የብቃት ማረጋገጫ በላይ ሲሰሩ መገኘት | - የመጀመሪያ ደረጃ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የተሰራው ስራ ስታንዳርዱን የጠበቀ ከሆነ ብቻ የምዝገባ አገልግሎት መስጠት | የ2ኛ ደረጃ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ጋራዡን ለሶስት ወር እንዲታገድ ማድረግና ስታንዳርዱን የጠበቀ ከሆነ ብቻ የምዝገባ አገልግሎት መስጠት | - የጋራዡን የብቃት ማረጋገጫ መሠረዝና አካል ማሳወቅ | |
| 3 | ከተፈቀደው የአገልግሎት ዘመን በላይ ላገለገሉ ተሽከርካሪዎች የአካል ለውጥ ሰርቶ መገኘት | - የብቃት ማረጋገጫውን ለ6 ወር ማገድና ተሽከርካሪው የምዝገባ አገልግሎት እንዳያገኝ ማድረግ፣ ተሽከርካሪውን ወደ ቀድሞ አካሉ እዲመልስ ማድረግ። | የብቃት ማረጋገጫውን ለ1 ዓመት ማገድና ተሽከርካሪው የምዝገባ አገልግሎት እንዳያገኝ ማድረግ | - የጋራዡን የብቃት ማረጋገጫ መሠረዝና ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ | |
| 4 | ተገቢው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ኖሮት በሀገራችን የተሽከርካሪ አካል ለውጥ እንዲሰራላቸው ከተፈቀደላቸው የተሽከርካሪ ሞዴሎች ውስጥ ላልተካተቱ ተሽከርካሪዎች ከፌደራል | - የጋራዡን ብቃት ማረጋገጫ ለ6 ወር ማገድና ተሽከርካሪው የምዝገባ አገልግሎት እንዲያገኝ ማድረግ እና ተሽከርካሪው ከስሌቱ ውጪ ከሆነ ምዝገባ እንዳያገኝ በማድረግ ወደ | - የጋራዡን ብቃት ማረጋገጫ ለ1 ዓመት ማገድና ተሽከርካሪው የምዝገባ አገልግሎት እንዳያገኝ ማድረግ | የጋራዡን የብቃት ማረጋገጫ መሰረዝና ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ትራንስፖርት ባለስልጣን እውቅና ውጪ የአካል ለውጥ ሰርቶ መገኘትና የአካል ለውጥ የተሠራለት ተሽከርካሪ በአካል ለውጥ መመሪያው መሠረት የመጫን አቅሙ ሲሰላ ሞዴሉ ለምዝገባ ብቁ መሆን ካልቻለ | ቀድሞ አካሉ እዲመልስ ማድረግ | | | |
| 5 | ተገቢው የጋራዥ ብቃት ማረጋገጫ ኖሮት በሀገራችን የተሽከርካሪ አካል ለውጥ እንዲሰራላቸው ከተፈቀደላቸው የተሽከርካሪ ሞዴሎች ውስጥ ላልተካተቱ ተሽከርካሪዎች ከባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ እውቅና ውጪ የአካል ለውጥ ሰርቶ መገኘትና የአካል ለውጥ የተሠራለት ተሽከርካሪ በአካል ለውጥ መመሪያ መሠረት የመጫን አቅሙ ሲሰላ ሞዴሉ ለምዝገባ ብቁ መሆን ከቻለና የአካል ለውጥ ስራውም ስታንዳርዱን የጠበቀ ከሆነ | - የመጀመሪያ ደረጃ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ | - የጋራዡን ብቃት ማረጋገጫ ለ3 ወር ማገድ | የጋራዡን የብቃት ማረጋገጫ ለ1 ዓመት ማገድ | - የጋራዡን የብቃት ማረጋገጫ መሠረዝና ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ |
| 6 | ተገቢው የጋራዥ ብቃት ማረጋገጫ ኖሮት በሀገራችን የተሽከርካሪ አካል ለውጥ እንዲሰራላቸው ከተፈቀደላቸው የተሽከርካሪ ሞዴሎች ውስጥ ላልተካተቱ ተሽከርካሪዎች ከባለሥልጣን | ስራውን በመስፈርቱ መስረት እንዲያስተካክል ተደርጎ የመጀመሪያ ደረጃ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል | የጋራዡን ብቃት ማረጋገጫ ለ3 ወር ማገድ | -የጋራዡን የብቃት ማረጋገጫ ለ1ዓመት ማገድ | - የጋራዡን የብቃት ማረጋገጫ መሠረዝና ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ |

አብዲሣ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | መስሪያ ቤቱ እውቅና ውጪ የአካል ለውጥ ሰርቶ መገኘትና የአካል ለውጥ የተሠራለት ተሽከርካሪ በአካል ለውጥ መመሪያ መሠረት የመጫን አቅሙ ሲሰላ ሞዴሉ ለምዝገባ ብቁ መሆን ከቻለና የአካል ለውጥ ስራው ማስተካከያ የሚያስፈልገው ሆኖ ሲገኝ | | | | |
| 7 | ለተሽከርካሪ አካል ለውጥ ከተቀመጠው ልኬት /ስፔስፊኬሽን/ በላይ ወይንም በታች አድርጎ የተሽከርካሪ አካል ለውጥ የሰራ | - የመጀመሪያ ደረጃ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ተሽከርካ ሪውን በስፔስፊኬሽኑ መሠረት እንዲያስ ተካክል ማድረግ | - ተሽከርካሪውን በስፔስፊኬሽኑ መሠረት እንዲያስተካክል ማድረግና የብቃት ማረጋገጫውን ለ3 ወር ማገድ | - የጋራዡን የብቃት ማረጋገጫ ለ1 ዓመት ማገድና የተሽከርካሪው አካል በስፔስፊኬሽኑ መሠረት እስካልተስተካከለ ድረስ ምዝገባ እንዳያገኝ ማድረግ | - የጋራዡን የብቃት ማረጋገጫ መሠረዝና ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ |
| 8 | የአገልግሎት ጊዜውን በጨረሰ (ባልታደሰ) የጋራዥ ብቃት ማረጋገጫ ተጠቅሞ የተሽከርካሪ ጥገና እና አካል ለውጥ መስራት | - ከ 7 ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ቀርበው እንዲያድሱ የመጀመሪያ ደረጃ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ እንዲደርሳቸው ማድረግ | የጋራዡን ብቃት ማረጋገጫ ለ3 ወር ማገድ | -የጋራዡን የብቃት ማረጋገጫ ለ1ዓመት ማገድ | የጋራዡን የብቃት ማረጋገጫ መሠረዝና ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ |
| 9 | የአካል ለውጥ ለማሰራት ለሚቀርብ የተሽከርካሪ ባለንብረት በጥገና እና አካል ለውጥ ዙሪያ መረጃ አለመስጠት ወይንም የተሣሣተ መረጃ መስጠት | - የመጀመሪያ ደረጃ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ | - የሁለተኛ ደረጃ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ | - የጋራዡን የብቃት ማረጋገጫ ለ6 ወር ማገድ | - የጋራዡን የብቃት ማረጋገጫ ለ1 ዓመት ማገድ |
| 10 | የብቃት ማረጋገጫ ሰጪው አካል እና ለባለሥልጣኑ ለድጋፍና ክትትል | -የመጀመሪያ ደረጃ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ | - የሁለተኛ ደረጃ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ | - የጋራዡን የብቃት ማረጋገጫ ለ6 ወር ማገድ | - የጋራዡን የብቃት ማረጋገጫ ለ1 ዓመት ማገድ |

አብዲሣ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ለሚያስማራቸው ባለሙያዎች ተገቢውን መረጃ አለመስጠት። | | | | |
| 11 | ህጋዊ ባልሆነ /በማስመሰል በተሰራ/ የጋራዥ ብቃት ማረጋገጫ ሲጠቀሙ መገኘት | በፈቃድ ሰጪው አካል የህግ አገልግሎት በኩል ክስ እንዲመሰረትበት ማድረግ | | | |
| 12 | ለጋራዡ የተሰጠውን የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ለሌላ ማንኛውም ዓይነት ጋራዥ አሳልፎ መስጠት | - የመጀመሪያ ደረጃ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ | - የጋራዡን የብቃት ማረጋገጫ ለ1 ዓመት ማገድ | - የጋራዡን የብቃት ማረጋገጫ መሠረዝ | |
| 13 | በጋራዡ ውስጥ ጥገና እና የአካል ለውጥ የተሠራላቸውን ተሽከርካሪዎች መረጃ እና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን መረጃዎች በተመለከተ በቋሚነት በየወሩ እንደአስፈላጊነቱ ደግሞ በተጠየቀበት ጊዜ ለብቃት ማረጋገጫ ሰጪው አካል በሪፖርት አለማሳወቅ | - የመጀመሪያ ደረጃ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ | -ሁለተኛ ደረጃ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ | - የጋራዡን የብቃት ማረጋገጫ ለ6 ወር ማገድ | የጋራዡን የብቃት ማረጋገጫ ለ1 ዓመት ማገድ |
| 14 | የጋራዥ ብቃት ማረጋገጫው [illegible]ተሰጠበት ወቅት [illegible]ረባቸውን አጠቃላይ የሰው [illegible]ል፣ የስራ መሳሪያ ፣ የስራ [illegible] እና የጤና መመዘኛዎች [illegible]ንገተኛ ክትትል [illegible]ሚደረግበት ወቅት አሟልቶ | - የመጀመሪያ ደረጃ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ | - የጋራዡን የብቃት ማረጋገጫ ለ6 ወር ማገድ | - የጋራዡን የብቃት ማረጋገጫ ለ1 ዓመት ማገድ | |

ታምሩ ያደታ ሁንዴ
ዋና ዳይሬክተር

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | አለመገኘት | | | | |
| 15 | በተለያዩ ምክንያቶች በጋራዡ ውስጥ ከ3 ወር ወይም ውል ከተዋዋሉበት ከ1 ወር በላይ ያለአግባብ የቆሙ ተሽከርካሪዎችን ለፈቃድ ሰጪው አለማሳወቅ | - የመጀመሪያ ደረጃ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ | - ሁለተኛ ደረጃ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ | - የጋራዡን የብቃት ማረጋገጫ ለ6 ወር ማገድ | - የጋራዡን የብቃት ማረጋገጫ ለ 1 ዓመት ማገድ |
| 16 | ተገቢው የጋራዥ ብቃት ማረጋገጫ ኖሮት ተሽከራካሪዎች በግጭትም ሆነ በግልበጣ አደጋ ለጥገና ወደ ጋራዥ በሚመጡበት ወቅት ስራ ከመጀመሩ በፊት የፖሊስ ማሰረጃ ወይም ይህ ካልሆነ ከፈቃድ ሰጪው አካል ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል | የጥገና ተቋሙ ባለንብረት በፈቃድ ሰጪው አካል የህግ አገልግሎት በኩል ክስ እንዲመሰረትበት ማድረግ ለፈቃድ ሰጭው ሳያሳውቅ የተሰራው ስራ ምንም ችግር የሌለውከሆነና ስታንዳርዱን የጠበቀ ከሆነ ብቻ አገልግሎት ላይ እንዲውል ማድረግ | | | |

**21.2.** የዕገዳ እና ስረዛ እርምጃዎች የጊዜ አቆጣጠር እርምጃው ከተወሰደበት ቀን ጀምሮ ይሆናል።

**21.3.** ለየጥፋት አይነቶቹ የተቀመጠው የመጨረሻ የቅጣት እርምጃ ከተወሰደ በኋላ ለሚታይ ተመሳሳይ ጥፋት ለደረጃው የተቀመጠው የመጨረሻው እርከን እርምጃ ይወሰዳል።

**21.4.** በተሰረዘ ወይም በታገደ የብቃት ማረጋገጫ ሲጠቀም በተገኘ የጋራዥ ባለንብረት ላይ በፈቃድ ሰጪው የህግ አገልግሎት በኩል ከሚመሰረትበት ክስ በተጨማሪ በዕገዳ ወይም በስረዛ ጊዜ ውስጥ ለሰራቸው ተሽከርካሪዎች የምዝገባ አገልግሎት የሚሰጠው ተሽከርካሪዎቹ መስፈርቱን ካሟሉ ብቻ ነው።

ቅጽ -1

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ**

**የ--------ትንስፖርት ቢሮ /ባለስልጣን/**

**ለተሽከርካሪ ጥገና እና አካል ለውጥ ስራ ጋራዥ**

**የሙያ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ትራንስፖርትን ስለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ ቁጥር------------ አንቀጽ----------በተሰጠው ስልጣንና ተግባር መሠረት የ--------ትንስፖርት ቢሮ /ባለስልጣን/ በ-----------ከተማ----------ክፍለ ከተማ ---------- ቀበሌ ---------- የቤት ቁጥር ለሚገኘው ለ-----------------የ------ደረጃ -------------------አገልግሎት ከ------------እስከ---------------የሚያገለግል ይህ ቋሚ/ጊዜያዊ የሙያ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በየአመቱ የሚታደስ ሆኖ ተሰጥቷቸዋል።

**ማህተም**

**ያዘጋጀው ሰራተኛ ስም-----------------------------ፊርማ------- ቀን -----------------**

**ኃላፊ ስም-----------------------------ፊርማ------- ቀን -----------------**

| ዕድሳት | ዕድሳት | ዕድሳት |
|---|---|---|
| የታደሰበት ቀን ----------------- | የታደሰበት ቀን ----------------- | የታደሰበት ቀን ----------------- |
| የሚያገለግለው ከ---------እስከ------------ | የሚያገለግለው ከ---------እስከ------------ | የሚያገለግለው ከ---------እስከ-------------- |
| የኃላፊ ስም--------------------- | የኃላፊ ስም--------------------- | የኃላፊ ስም--------------------- |
| ፊርማ---------- | ፊርማ---------- | ፊርማ---------- |
| ማህተም | ማህተም | ማህተም |

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Transport Authority No. 1



አብዲሳ ያደታ ሙለታ
ዋና ዳይሬክተር

ቅጽ-2

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የ--------ትንስፖርት ቢሮ /ባለስልጣን/

ለተሽከርካሪ ጥገና / አካል ለውጥ ስራ ጋራዥ አገልግሎት

የሙያ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ጥያቄ ማቅረቢያ በባለጉዳይ የሚሞላ ማመልከቻ ቅጽ

1. የድርጅቱ ባለንብረት ስም ------------------------------------
2. ድርጅቱ የሚገኝበት አድራሻ

   ከተማ ----------- ክፍለ ከተማ ------------- ስልክ ቁጥር ------------------

   ቀበሌ ---------------------------- ፓስታ ሳ.ቁ ---------------

   የቤት ቁጥር -------------------- የአካባቢ ልዩ መገለጫ -------
3. የሥራ አስኪያጅ ስም -----------------------------------
4. የሚጠይቁት ድርጅት አገልግሎት አይነት ------------------ ደረጃ ----------------------
5. የቦታ ሁኔታ ---------------------------- (ካርታውን ኮፒ ያያይዙ) የቦታው ስፋት --------------
6. ቦታው የኪራይ ከሆነ ህጋዊ የኪራይ ውል ቢያንስ ለአንድ አመት የሚያገለግል ያያይዙ
7. የድርጅቱ የስራ ቦታ፣ ቢሮና የጥገና ክፍሎች መግለጫ

| ተ.ቁ | የስራ ክፍሎች ዝርዝር | መጠን (Dimension) | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |

8. የጤናን ችግር ወይም አደጋን ለመከላከል በድርጅቱ የተዘጋጀ መሣሪያ

| ተ.ቁ | የመሳሪያ ዝርዝር | ብዛት | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| | | | |

9. በድርጅቱ ውስጥ ያለውን የሰው ሃይል በተመለከተ የትምህርት ደረጃና የስራ ልምድ ከህጋዊ የሠነድ ኮፒ ጋር በሚከተለው ሰንጠረዥ ዓይነት ሞልተው ያቅርቡ

| ተ.ቁ | የሠራተኛው ስም | የስራ ድርሻ | የት/ደረጃ | የስራ ልምድ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |

10. በየድርጅቱ ውስጥ ያሉትን መሳሪያዎች በሚከተለው ሠንጠረዥ ዓይነት ሞልተው ያቅርቡ

| ተ.ቁ | የመሣሪያው ዓይነት | ብዛት | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| | | | |

11. መረጃውን የሰጠው የድርጅቱ ኃላፊ ወይም ህጋዊ ተወካይ

    ስም ------------------------------------ፊርማ -----------------------ቀን-----------------------

የድርጅቱ ማህተም



አብዲሣ ያደታ ሙሊታ
ዋና ዳይሬክተር

34

ቅጽ-3

## ለተሽከርካሪ አካል ለውጥና ሞዴፊክ ሥራ/ጥገና/ ጋራዥ አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለሚጠይቁ ግዴታ መግቢያ

እኔ አቶ/ወይዘሮ---------------------------------- የ ------------------ ጥገና/ አካል ለውጥ ስራ ጋራዥ ባለቤት/ህጋዊ ተወካይ የሆንኩ በ-------------------ከተማ-------------------ክ/ከተማ-------------------ቀበሌ-- -------------------------የቤት ቁጥር የአከባቢው ልዩ መገለጫ------------------------------በሆነ------------- ------------------------ አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሲሰጠኝ በግምገማ ወቅት የተመዘገቡትን አደረጃጀት፣የሰው ኃይልና የስራ መሳሪያ ሳላጓድል ልሰራ እንድሁም ማንኛውም ለውጥ ስኖር ለብቃት አረጋጋጭ ፈቃድ ሰጭ ትራንስፖርት መ/ቤት የማሳውቅ መሆኑን እየገለጽኩ መስፈርቱን ጠብቄ አገልግሎት ልሰጥ ግዴታ መግባቴን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም---------------------------------

ፊርማ-----------------------------------

ቀን---------------------------------

**የድርጅቱ ማህተም**

Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Transport Authority No. 1